# ርዕሰ አንቀጽ

## ድርቅና ጠኔ ከምርምር አንጻር ሲታይ

ስለድርቅና ስለጠኔ በምርምር ደረጃ በምንነጋገርበት ጊዜ ከተራ ገለጻ ማደ ዘልቀን ጠለቅ ወዳለ ትንተና እንገባለን። በተራ አነጋገር የድርቅና የጠኔ እንዲሁም አብረው ተከትለው የሚሄዱት ችግሮች ሁሉ መንስኤና እንዴት፣ ለምንና ለማን የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ አይደሉም። በጽሑፍ ደረጃ አያሌ ድርሰቶች በምርምር ላይ ያልተመሠረቱ፤ ጥልቅ ጥናት ያልተደረገባቸው ሐሳቦችን አዝለው ይወጣሉ። በዚህ ደረጃ የሚሰነዘሩ መንስኤዎችም ሆኑ መፍትሄዎች በሃገር ደረጃ ሊወሰዱ ለሚገባቸው እርምጃዎች እምብዛም የሚያገለግሉ አይሆኑም። አገልግሎት ላይ ቢውሉም አገልግሎታቸው መሠረታዊ መፍትሄ በማበርከት ደረጃ ሲታይ አይችልም ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ምርምርና ጥናት የተደረገባቸው ድርሰቶች ስለድርቅና ስለጠኔ እንዲሁም አብረው ስለሚሄዱት እክሎች ሁሉ መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖረን ከመርጃታቸውም ሌላ መፍትሄም ለመዘየድ አመቺ ሁኔታን ያዘጋጃሉ። በተጨማሪም ጠቃሚ የሆነ የዕውቀትና የምርምር ዘዴ ክምችት እንዲኖር ይረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የምድር መድረቅ ብቻ ሳይሆን የሐሳብና የአስተሳሰብ ድርቅ ሰፍኖ ይገኛል። አስቸኳይ እርምጃዎችና መፍትሄዎች በሚያስፈልጉባቸው አንዳንድ



Harergie Ethiopic Typeface